# አዛውንቶች ራሳቸውን ችለው የሚኖሩበት ፕሮግራም

በፍራንክሊን ካውንቲ ለሚኖሩ ዕድሜአቸው ከ60 ዓመት በላይ ለሆኑ አዛውንቶች ራሳቸው ችለው መኖር እንዲችሉ የመረጃ ምንጭና አገልግሎት የሚሰጥ ፕሮግራም ነው።

**አዛውንቶች የሚቀርብላቸው ፕሮግራምና አገልግሎቶች፣**

- ☐ የመረጃ ማግኘት
- ☐ ጉዳያቸውን ተከታትሎ የማስፈፀም
- ☐ የቤት ውስጥ የስራ እገዛ
- ☐ የግል ንጽህና መጠበቅ
- ☐ እንክብካቤ በቀጣይነት የማግኘት አገልግሎት
- ☐ በአደጋ ጊዜ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ማሳወቅ
- ☐ የበሰለ የምግብ አገልግሎት በየመኖርያ ቤት ማግኘት
- ☐ ወደሕክምና የማመላለሻና ማጓጓዣ አገልግሎት
- ☐ የአዛውንቶች ክበብ
- ☐ ጥቃቅን የቤት ጽገና ስራ
- ☐ የአሜሪካ ዜግነት ትምህርትና ለፈተና ማዘጋጀት

ከላይ የተጠቀሱትን አገልግሎቶች ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለጉ እናንተን በቋንቋችሁ ለማገልገል የተዘጋጁ ብቃት ያላችው ጉዳይ አስፈፃሚዎች በነፃ አገልግሎት ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እየገለጽን የቢሮ የስራ ሰዓታችን እንደሚከተለው ነው።

የስራ ሰዓት   ከሰኞ - ዐርብ   8:30 a.m. - 4:30 p.m.

ስልክ **(614) 235-5747**

አድራሻችን፣

3624 Bexvie Avenue, Columbus, OH 43227

FRANKLIN COUNTY
Senior Options

**Franklin County Office on Aging**

*an agency of the*

**Franklin County Board of Commissioners**

www.officeonaging.org

# ለአዛውቶች የሚሰጡ አገልግሎቶች

**መረጃ ማግኘት፡** ለአዛውቶች አስፈላጊ የሆኑትን የመረጃዎች ማመልከትና አስፈላጊውን እርዳታ መስጠት።

**ጉዳያቸውን ተከታትሎ ማስፈጸም፡** በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞች ያላቸውን ጉዳይ አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ ጉዳዩን ማስፈጸም።

**የቤት ውስጥ የስራ እገዛ** ጥቃቅን የቤት ውስጥ የስራ እገዛ እንድያገኙ መርዳት።

**የግል ንጽህና መጠበቅ፡** አዛውቶችን የግል ንጽህና የመጠበቅ ጠቀሜታ ማስተማርና የግል ንጽህና መጠበቅያ የሚያገኙበት ዘዴ መፈለግ።

**አገልግሎት በቀጣይነት ማግኘት፡** አዛውንቶች ለወደፊቱ ያለማቋረጥ አገልግሎት እንዱያገኙ መከታተልና ማረጋገጥ።

**በአደጋ ጊዜ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች፣** አዛውንቶች አደጋ ሲያጋጥማቸው ማድረግ ያለባቸውን እርምጃዎች ማስተማርና ማሳወቅ።

**የበሰለ ምግብ አገልግሎት፡** አዛውንቶች የበሰለ ምግብ ማግኘት በፈለጉ ጊዜ በስለው የተዘጋጁ የምግብ አቅርቦት ከሚመለከተው አካል ግኑኝነት በመፍጠር አቅርቦት እንዲያገኙ ማድረግ።

**የትራንስፖርት ማጓጓዣ አገልግሎት፡** አዛውንቶች ለሕክምናና ለግል ጉዳያቸው የትራንስፖርት አገልግሎት የሚያገኙበት መንገድ ማመቻቸት።

**የአዛውንቶች ክበብ፡** በአካላዊ ብቃት ማነስ የመንቀሳቀስ ችግር ለሚያጋጥማቸው የተሟላ የጤና አገልግሎትና የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

**ጥቃቅን የቤት ጥገና፡** አዛውንቶች በመኖርያ ቤታቸው ውስጥ አስፈላጊ ጥቃቅን ጥገና እንዲያገኙ ማድረግ።

**ለዜግነት ትምህርት፣** የአሜሪካን ዜግነት ማግኘት ለሚፈልጉ አዛውንቶች ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ጋር በመሆን እገዛ መስጠትና የዜግነት ትምህርት በመስጠት ለፈተና በማዘጋጀት እንዲያገኙ ማድረግ።